**እስራኤል አገር**

**የትምህርት ሚኒስቴር**

**የፈተናው ዓይነት፦** የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መልቀቂያ ፈተና

**የፈተናው ጊዜ፦** የ2018 ዓ.ም. የክረምት ፈተና

**የፈተናው ቁጥር፦ 034284, 034202, 176**

**ወደ አማርኛ የተተረጎመ** (6)

# *ሥነ-ዜጋ*

## ለአዲስ ገቢዎች

## ለውጤታማ ትምህርት በተዘጋጀው የሪፎርም ዕቅድ መሠረት

### ለተፈታኙ የቀረቡ መመሪያዎች

א. <u>ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ</u>፦ ሁለት ሰዓት ተኩል።

ב. <u>የፈተናው መዋቅርና የነጥብ አሰጣጥ</u>፦

ይህ ፈተና ሁለት ምዕራፎች አሉት።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምዕራፍ አንድ | — | (2x32) | — 64 ነጥብ |
| ምዕራፍ ሁለት | — | (3x12) | — 36 ነጥብ |
| | | በአጠቃላይ | — 100 ነጥብ |

ג. <u>ለመጠቀም የተፈቀደ የመርጃ መሣሪያ</u>፦

የውጭ ቋንቋ-ዕብራይስጥ/ዕብራይስጥ-የውጭ ቋንቋ መዝገበ ቃላት።

ד. <u>ልዩ መመሪያ</u>፦

ጥያቄውን ከመመለስህ በፊት በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የተሰጠውን መመሪያ በጥሞና አንብብ።

ሥራህን በሙሉ <u>በዚህ የፈተና ደብተር ላይ ብቻ</u> ጻፍ። የፈተናውን <u>ረቂቅ</u> <u>(טיוטה)</u፣ ርዕሶችንና የመሳሰሉትን በተለዩ ገጾች ላይ ጻፍ። በእያንዳንዱ የረቂቅ ገጽ ላይ "ረቂቅ"ብለህ ከላይ ጻፍበት። ማንኛውንም ረቂቅ በሌላ ወረቀት ላይ መጻፍ የፈተናውን ውድቅ መሆን ሊያስከትል ይችላል።

**በዚህ ፈተና ውስጥ የፈተናው መመሪያዎች በወንድ ጾታ ቢቀርቡም ለሁለቱም ጾታዎች ያገለግላሉ።**

## መልካም ዕድል!

**מדינת ישראל**

**משרד החינוך**

סוג הבחינה: בגרות

מועד הבחינה: חורף תשע"ח, 2018

**מספר השאלון: 176 , 034202 , 034284**

**תרגום לאמהרית (6)**

# אזרחות

## לעולים חדשים

## על פי תכנית הרפורמה ללמידה משמעותית

### הוראות לנבחן

א. <u>משך הבחינה</u>: שעתיים וחצי.

ב. <u>מבנה השאלון ומפתח ההערכה</u>:

בשאלון זה שני פרקים.

| | | | |
|---|---|---|---|
| פרק ראשון | —(32x2) | — | 64 נקודות |
| פרק שני | —(12x3) | — | 36 נקודות |
| סה"כ | | — | 100 נקודות |

ג. <u>חומר עזר מותר בשימוש</u>:

מילון עברי-לועזי / לועזי-עברי.

ד. <u>הוראה מיוחדת</u>:

לפני שתענה, קרא בעיון את ההוראה בראש כל פרק.

כתוב <u>במחברת הבחינה בלבד</u>, בעמודים נפרדים, כל מה שברצונך לכתוב <u>כטיוטה</u> (ראשי פרקים, חישובים וכדומה). רשום "טיוטה" בראש כל עמוד טיוטה. רישום טיוטות כלשהן על דפים מחוץ למחברת הבחינה עלול לגרום לפסילת הבחינה!

**ההנחיות בשאלון זה מנוסחות בלשון זכר ומכוונות לנבחנות ולנבחנים כאחד.**

## בהצלחה!

# ጥያቄዎች

## ምዕራፍ አንድ (64 ነጥብ)

ከ1-3 ካሉት ጥያቄዎች መካከል ሁለቱን መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ – 32 ነጥብ)።

**1.** እስራኤል አገር — ይሁዳዊት አገር

ሀ. **የአገሪቱ የሕዝብ መዝሙር** ("ሃቲክቫ") እና **የአገሪቱ ምልክት** (סמל המדינה) እንዴት የእስራኤልን አገር ይሁዳዊ ገጽታ እንደሚገልጹ አብራራ።
(12 ነጥብ)

ለ. በነጻነቱ አዋጅ ላይ የእስራኤል አገር ይሁዳዊ ገጽታ ተግባራዊ ሆኗል። ከአዋጁ ውስጥ የእስራኤልን አገር ይሁዳዊ ገጽታ የሚገልጹ ሁለት ምሳሌዎችን አብራራ። (12 ነጥብ)

ሐ. የዜግነት ሕግ የእስራኤል አገር ይሁዳዊ ገጽታን እንዴት እንደሚገልጸው አብራራ።
(8 ነጥብ)

**2.** ፓርላማው (הכנסת)

ሀ. የፓርላማውን ሁለት የሥራ ድርሻዎች አብራራ። (8 ነጥብ)

ለ. በፓርላማው ውስጥ **ጥምር መንግሥት** (קואליציה) ምን እንደሆነ እና **የተቃዋሚ ፓርቲ** (אופוזיציה) ምን እንደሆነ አብራራ። (12 ነጥብ)

ሐ. የፓርላማ ምርጫ ዘዴ **ሃገራዊ-ዝርዝራዊ-አንጻራዊ** (ארצית־רשימתית־יחסית) ነው። የዚህን ዘዴ ሦስት ክፍሎች እያንዳንዳቸውን አብራራ። (12 ነጥብ)

**3.** የሰው ልጅ መብቶች (זכויות אדם)

ሀ. የተፈጥሮ መብቶች (זכויות טבעיות) ምን እንደሆኑ አብራራ። (8 ነጥብ)

ለ. የሰውን ልጅ መብቶች እና የዜጋን መብቶች መገደብ የሚቻለው መቼ እንደሆነ አብራራ።
(12 ነጥብ)

ሐ. ከፊትህ ያለውን ክፍል አንብብ እና ቀጥሎ ባሉት ሁለት ጥያቄዎች ላይ መልስ ስጥ።

**የእስራኤል አገር ሕግ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሠጡ ቦታዎችን በሙሉ፣ ለምሳሌ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች እና የመዝናኛ ቦታዎች፣ ለአካል ጉዳተኞች በተሽከርካሪ ወንበር ለሚንቀሳቀሱ አካለ-ስንኩላን እና ለዓይነ-ስውራን ተስማሚ የመሆን ግዴታ እንዳለባቸው ወስነዋል። የዚህ ሕግ ዓላማ በእንደነዚህ ዓይነት ቦታዎች ሁሉም ሰው ገብቶ እንደማንኛውም ሰው አገልግሎት መቀበል እንዲችል ለማድረግ ነው።**

– የእኩልነትን መብት አብራራ።
– የእኩልነት መብት በክፍሉ ውስጥ እንዴት እንደተገለጸ አብራራ።

(12 ነጥብ)

/ገጽ 3 ላይ ይቀጥላል/

## ምዕራፍ ሁለት (36 ነጥብ)

ከ4-8 ካሉት ጥያቄዎች ውስጥ ሦስቱን በአጭር በአጭሩ መልስ (ለእያንዳንዱ ጥያቄ – 12 ነጥብ)።

**4.** የስታተስ ኮዎ ስምምነት (הֶסדר הסטטוס־קוו) ምን እንደሆነ አብራራ እና ይህ የሚሠራባቸውን ሁለት ርዕሶች ጥቀስ።

**5.** የመንግሥት የጋራ ኀላፊነት (האחריות המשותפת) ምን እንደሆነ አብራራ።

**6.** የብዙኀን መገናኛ በመንግሥት ላይ ግምገማ (פיקוח) እና ቁጥጥር (ביקורת) የሚያደርግባቸውን ሁለት መንገዶች አብራራ።

**7.** የሚከተሉትን ሁለት ጽንሰ-ሐሳቦች አብራራ፦

– የሕዝብ ሥልጣን ደምብ/የሕዝብ ሉዓላዊነት (עקרון שלטון העם)

– የፕሬዝዳንታዊ አስተዳደር (ממשל נשיאותי)

**8.** የወረዳው ፍርድ ቤት (בית משפט מחוזי) የሚሠራቸውን ሁለት ጉዳዮች አብራራ።

**መልካም ዕድል!**

መብቱ የእስራኤል መንግሥት ነው።
መገልበጥም ሆነ ማባዛት እንዲሁም ማሳተም በት/ሚኒስቴር ፈቃድ ብቻ ነው።

**בהצלחה!**

זכות היוצרים שמורה למדינת ישראל
אין להעתיק או לפרסם אלא ברשות משרד החינוך